

# የፈቃድ መስጫ ገለጻ
# ለአዲስ የልጅ እድገት ማዕከላት

# መግቢያ

# መግቢያ

- እንኳን ወደ የስቴት ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (ኦፊስ ኦፍ ዚ ስቴት ሱፐርኢንተንደንት ኦፍ ኤጁኬሽን) (ኦ.ኤስ.ኤስ.ኢ.) (OSSE) የልጅ እንክብካቤ ፍቃድ መስጫ የኢንተርኔት ላይ ገለጻ በደህና መጡ።

- ፍቃድ ያገኙ የልጅ እድገት አቅራቢዎች በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ደህንነት ያለው፣ ጤናማ እና አሳዳጊ እንክብካቤን ለልጆች ያቀርባሉ። እርስዎ ፍቃድ ያለው አቅራቢ ለመሆን ላሳዩት ፍላጎት እናመሰግናለን።

- ይህ ገለጻ ለማጣናቀቅ በግምት 1 ሰዓት ይወስዳል። ይህ የፍቃድ መስጫ መስፈርቶች እና የፍቃድ መስጫ ሂደት አጠቃላይ እይታ ነው። እርሱ ሁሉንም ደንቦች ወይም መስፈርቶችን አያካትትም፣ ስለዚህ ሁሉንም የፍቃድ መስጫ ደንቦችን መከለስዎ አስፈላጊ ነው።

- እባክዎ ያስታውሱ፥ ልዩ ፍላጎቶች እና/ወይም የቋንቋ ተደራሽነት የሚያስፈልጋቸው እጩ አመልካቾች ከፈቃድ ሰጪ ቡድን ጋር የአንድ-ለአንድ ገለጻ እንዲደረግላቸው ቀጠሮ ማስያዝ ይችላሉ። ለበለጠ መረጃ እና ጥያቄዎች፣ እባክዎ የፈቃድ ሰጭ ቡድኑ ጋር በ (202) 727-1839 ይደውሉ እና በሥራ ላይ ያለውን የፈቃድ ሰጭ ስፔሺያሊስትን ለማነጋገር ይጠይቁ።

# መመሪያዎች

- ለገለጻ ክፍለ-ጊዜ ለመዘጋጀት፣ እባክዎ ከታች ያለውን ማስፈንጠሪያ በመጠቀም ለልጅ እድገት ተቋማት ፍቃድ መስጫ የመጨረሻ የሕግ-ማውጫን (የመጨረሻ የሕግ-ማውጣት) ያውርዱ።

  osse.dc.gov/sites/default/files/dc/sites/osse/publication/attachments/Final%20Rulemaking%20for%20the%20Licensing%20of%20Child%20Development%20Facilities.pdf

- በመላው ገለጻ ወቅት የደንብ ቁጥሮች የስላይዶቹ የታችኛው የቀኝ ጥግ ላይ ተጠቅሰዋል። እባክዎ የመጨረሻ የሕግ-ማውጫ ውስጥ የማመልከቻ ደንቦችን ለመገምገም እነዚህን መጠቁሞች ይጠቀሙ።
- እያንዳንዱን ስላይድ ሙሉ በሙሉ ያንብቡ እና ጥያቄዎችዎን ይጻፉ።
- ገለጻውን አንዴ ካጠናቀቁ በኋላ፣ የፈተናውን ውጤቶች ያትሙ።
- ገለጻውን ካጠናቀቁ በኋላ፣ ጥያቄዎችዎን እንዲመልስልዎ በስራ ላይ ያለውን የፍቃድ መስጫ ስፔሻሊስትን ለማነጋገር ነጻነት ይሰማዎት። የፍቃድ መስጫ ክፍልን ለማነጋገር፣ እባክዎ ወደ (202) 727-1839 ይደውሉ

# የአዲሱ ደንቦች ዓላማ

- በዲሴምበር 2, 2016፣ OSSE በ*D.C. Register* (63 *DCR* 50) ውስጥ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት በሙሉ የልጆችን ዕድገት ተቋማት ፈቃድ መስጫን የሚገዙ ሕጎችን በማሻሻል የመጨረሻውን የሕግ-ማውጫ ማስታወቂያን አሳትሟል።

- የመጨረሻው የሕግ-ማውጫ ዓላማ በዲስትሪክቱ ውስጥ ፈቃድ በተሰጠው የልጆች እድገት ተቋም እየቀረበ ያለው እንክብካቤ እና ትምህርት ደኅንነቱ የተጠበቀ እንደሆነ ለማረጋገጥ፣ እና በልጆች እንክብካቤ ላይ ጤናን፣ ደኅንነት፣ መልካም መሆን፣ እና ልጆች በእንክብካቤ ውስጥአዎንታዊ ዕድገት እንዲኖራቸው ለመጠበቅ የልጆቹን ጤናማ ዕድገት፣ የወደፊቱ በትምህርት ላይ የሚያስመዘግቡት ውጤት እና ስኬትን ይረዳል።

- የመጨረሻው የሕግ አውጪ ቅርብ ጊዜ የተደረገውን ምርምር እና በልጆች ዕድገት ውስጥ ምርጥ ልምምድን ለማንጸባረቅ፣ የፌደራል የልጅ እንክብካቤ እና እድገት የእርዳታ ብሎክ አዋጅ 2014 (CCDBG Act) ለመከተል፣ እና የልጆች ዕድገት ተቋማት ላይ ተጽእኖ የሚያደርግ የዲስትሪክቱ ህጎች እና ደንቦች ጋር ለማስተባበር የግዛቱን የሕግ ማዋቅር ያሻሽላል።

# የገለጻ (ኦሪየንቴሽን) አጀንዳ

1. ፍቃድ መስጠት ላይ ስለ OSSE ሚና
2. የልጅ እድገት ማዕከል ትርጉም
3. የፍቃድ መስጫ ደንቦች
4. የፍቃድ መስጫ መታለፎች
5. የቦታ መስፈርቶች
6. የሠራተኛው ብቃቶች
7. የቁጥጥር መስፈርቶች
8. ጤና፣ ደህንነት እና ጤንነት
9. ግብአቶች እና ድጋፎች
10. የፍቃድ መስጫ የጊዜ ገደብ
11. የፈቃድ አሰጣጥ ሂደት
12. የገለጻ መጠይቅ

# የOSSE ሕግ

# የልጅ እድገት ተቋም ፍቃድ

- በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ የልጅ እድገት ተቋም ፈቃድ የሚወጣው በ OSSE የቀደመ ትምህርት (ኤርሊ ለርኒንግ) ክፍል (Division of Early Learning (DEL)) ነው።
- OSSE በዲስትሪክቱ ውስጥ ለልጅ እንክብካቤ ፍቃድ መስጫ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ነው እና ፍቃድ ያላቸው ተቋማት ውስጥ አገልግሎት የሚወስዱ ልጆች ጤና፣ ደህንነት፣ ጤንነት እና አዎንታዊ እድገትን ለማረጋገጥ ለልጅ እድገት ተቋማት ፍቃድ ለመስጠት እና ለመቆጣጠር ሀላፊነት አለበት።

5A DCMR ምዕራፍ 1፣ 100

# የልጅ የእድገት ማዕከል ትርጉም

# የልጅ የእድገት ማዕከል ትርጉም

የልጅ እድገት ማዕከል ማለት ከተቋሙ ሥራ እስኪያጁ መኖሪያ ውጪ የሆኑ ህንጻዎች/ግቢዎች ውስጥ የሚገኝ እና ከ12 በላይ ህጻናትን የሚያገለግል ተቋም ማለት ነው።

ይህ ትርጓሜ በአጠቃላይ የልጅ እንክብካቤ ማእከላት፣ የቅድመ-ትምህርት ቤቶች፣ የነርሰሪ ትምህርት ቤቶች፣ የትምህርት ቤት በፊት እና በኋላ ፕሮግራሞች ተብለው የሚታወቁ ተቋማት፣ እና ተመሳሳይ ፕሮግራሞችን እና ተቋማትን ያቅፋል።

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1, 199፥

# የፍቃድ መስጫ ደንቦች

# የፍቃድ መስጫ ደንቦች

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የልጅ እድገት ተቋም ደንቦች የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የማዘጋጃ ቤት ደንቦች (ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሙኒሲፓል ሬጉሌሽንስ) (District of Columbia Municipal Regulations (DCMR))፣ ርዕስ 5A፣ ምዕራፍ 1 ውስጥ ተዘርዝረዋል።

የፍቃድ መስጫ ማመልከቻ ሂደቱን ከመጀመርዎ በፊት፣ የDCMR፣ ርዕስ 5A፣ ምዕራፍ 1 ይገምግሙ። ደንቦቹን መረዳት የፍቃድ መስጫ ሂደቱን በተሳካ ሁኔታ የማሰስ እና የተቋም ፍቃድ መስጫን በተሳካ ሁኔታ የማጠናቀቅ አስፈላጊ አካል ነው።

የፍቃድ መስጫ ደንቦች ማጠቃለያ በሚከተለው ማስፈንጠሪያ ይገኛል፥ osse.dc.gov/publication/summary-and-overview-final-rulemaking-licensing-child-development-facilities።

# የፍቃድ መስጫ መታለፎች

# የፍቃድ መስጫ መታለፎች

የሚከተሉት የልጅ እድገት አገልግሎቶች ተቋምን ለማሰራት ፍቃድ ከማግኘት የታለፉ ናቸው፥

- የልጅ ጠባቂ ቤት ወይም የአንድ ቤተሰብ የልጅ ቤት ውስጥ አልፎ አልፎ ልጅን መጠበቅ፤
- ለተንከባካቢ በልጁ ቤተሰብ ክፍያ እየተከፈለ በልጅ ቤት ውስጥ የሚሰጥ እንክብካቤ
- በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እንደተገለጸው፣ የልጅ ሞግዚት በመጋራት(ናኒ ሼር) ከአንድ በላይ ለሆኑ ልጆች የሚሰጥ እንክብካቤ፤
- መደበኛ ያልሆነ ወይም አልፎ አልፎ በወላጆች ቁጥጥር የሚደረጉ የልጆች የጨዋታ ቡድን፤
- አባላት አገልግሎቶችን መጠቀም እንዲችሉ ጊዜያዊ የልጅ ጥበቃ እንክብካቤን እንደ ጥቅማ ጥቅም የሚያቀርቡ የአዋቂ ጂሞች ወይም ክለቦች፤
- ወላጅ(ጆች) በተመሳሳይ ካምፓስ ውስጥ በሚቆዩበት ወቅት ልጁ በጊዜያዊነት ሲማር ወይም የትምህርት ፕሮግራም ሲከታተል የልጅ እንክብካቤ አገልግሎቶችን የሚያቀርቡ የአዋቂ ትምህርት ፕሮግራሞች፤

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1፣ 101.5፥

OSSE

# የፍቃድ መስጫ መታለፎች

የሚከተሉት የልጅ እድገት አገልግሎቶች ተቋምን ለማሰራት ፍቃድ ከማግኘት የታለፉ ናቸው፦

- ልጅን ማዕከል ያደረጉ የንግድ ሥራዎች ማስጠናት፣ ሙዚቃ፣ ዳንስ፣ ስፖርት፣ ወይም አርትን ጨምሮ ሌሎች ሴሽኖችን፣ ክፍሎችን ወይም እንቅስቃሴዎችን ወላጅ(ጆች) ወይም ሞግዚት(ቶች) የንግድ ሥራው በሚሰራበት ቅጥር ግቢ ውስጥ ባሉበት የሚሰጡ፤
- በሃይማኖታዊ አገልግሎቶች ወቅት በአምልኮ ቦታዎች ላይ የሚሰጥ እንክብካቤ፤
- በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እንደተገጸው፣ በተዛማጅ ሰው የቀረበ እንክብካቤ፤
- በፌዴራል መንግሥት ንብረት ላይ በፌዴራል መንግሥት የሚተዳደሩ ተቋሞች፣ ነገር ግን በፌዴራል መንግሥት ንብረት ውስጥ ወይም ቦታ ላይ ቦታ የሚጠቀም የግል አካል የፌደራል ህግ በግልጽ ከኮሎምቢያ ዲስትሪክት የቁጥጥር ስልጣን ነጻ ካላደረገው በስተቀር ከግዴታው ነጻ አይደለም፤

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1፣ 101.5፥

# የፍቃድ መስጫ መታለፎች

የሚከተሉት የልጅ እድገት አገልግሎቶች ተቋምን ለማሰራት ፍቃድ ከማግኘት የታለፉ ናቸው፥

- ከቅድመ መዋዕለ ህጻናት 3 ጀምሮ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ ለተማሪዎች የሙሉ ቀን ትምህርት አገልግሎት የሚሰጡ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የህዝብ ትምህርት ቤት ወይም የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት፤
- ከቅድመ መዋዕለ ህጻናት ጀምሮ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል 12 ድረስ ተማሪዎች የሙሉ ቀን ትምህርት አገልግሎቶችን የሚሰጡ የግል ትምህርት ቤቶች፤
- በ2008 የቅድመ-መዋዕለ ህጻናት መጨመሪያ እና ማስፋፊያ ህግ መሠረት የመዋዕለ ህጻናት የትምህርት አገልግሎቶችን ብቻ በመዋዕለ ህጻናት እድሜ ክልል ላሉ ልጆች የሚሰጡ፣ በOSSE የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው፣ ማህበረሰባዊ መሠረት ያላቸው ተቋማት፤
- እድሜያቸው ለትምህርት ለደረሱ ልጆች የቅድመ ትምህርት ቤት እንክብካቤ ብቻ፣ የድህረ ትምህርት ቤት እንክብካቤ ብቻ፣ ወይም የበጋ ካምፕ አገልግሎት ብቻ የሚሰጡ ተቋማት።
- በሌላ መንገድ በህግ የታለፉ ተቋማት።

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1፣ 101.5፥

# የበታ መስፈርቶች

# የቤት ውስጥ የቦታ መስፈርቶች

የቤት ውስጥ የፕሮግራም ቦታ ጽዱ፣ ንጽህና ያለው፣ ደህንነት ያለው እና በጥሩ የተጠገነ ተደርጎ መያዝ አለበት። ሁሉም ቦታዎች አደገኛ ከሆኑ ቁሳቁሶች ነጻ መሆን አለባቸው፣ እና መርዛማ የሆኑ ነገሮች (ማለትም፣ ቀለም፣ የማጽጃ አቅርቦቶች፣ ወዘተ.) ማስቀመጫ ሁል ጊዜ መቆለፍ አለበት።

ተቋማቱ የመከተለውን ቦታ መያዝ አለባቸው፥

- በአንድ ጨቅላ ህጻን 45 ስኩዌር ጫማ የፕሮግራም ቦታ
- 35 ስኩዌር ጫማ በአንድ ታዳጊ እና ልጅ (ያልተገደበ ቦታ)
- 45 ስኩዌር ጫማ በአንድ ልጅ (የተገደበ ቦታ)
- አንድ መጸዳጃ ቤት እና የውሃ ማፍሰሻ በ10 ልጆች
- ለብቻ የተለየ የሠራተኞች የማረፊያ ክፍል ያስፈልጋል
- ለታመሙ ልጆች ለብቻ ማውጫ አካባቢ
- በእድሜ-ተገቢ አሻንጉሊቶች፣ እና የቤት ውስጥ እቃዎች፣ ደህንነት ያላቸው፣ ጥሩ ጥገና ላይ የሚገኙ፣ ንጹህ እና መርዛማ ያልሆኑ፣ ወዘተ.

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1፣ 122 123፥

# የቤት ውስጥ ቦታ

ከ2 ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት፣ ወይም አምቡላንቶሪ-ውስጥ የሌሉ ልጆች፣ ቦታ ብቻ መያዝ ይችላሉ፥

- በጎዳና ላይ ደረጃ፤ እና
- እሱ ሁለት የመውጫ መንገዶች አሉት።

የመውጫ መንገዱ ደረጃዎች ካሉት፣ ሰራተኞች ህጻናትን የቤት መልቀቂያ አልጋዎች ወይም ጠፍጣፋ ጋሪዎች ውስጥ፣ በድንገተኛ ሁኔታ ጊዜ ለመንዳት፣ እንዲያስቀምጡ የሚያስችሉ ራምፖች ይኖረዋል። በማንኛውም መውጫ ላይ የራምፕ አለመኖር በእሳት አደጋ እና የድንገተኛ ሁኔታ የህክምና አገልግሎቶች (Fire and Emergency Medical Services) (FEMS) ከጸደቀ በኋላ።

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1, 163፥

# የቤት ውጭ ቦታ

ሁሉም ልጆች ደህንነት ያለው፣ ለእድገት ተገቢ የሆነ የቤት ውጪ አካባቢ ውስጥ ለቤት ውጭ ጨዋታ መደበኛ እድሎች ሊሰጣቸው ይገባል።

የቤት ውጪ የመጫወቻ ቦታ በህንጻዎቹ ላይ ከሌለ፣ አቅራቢው ሁሉም የተመዘገቡ ልጆች በአቅራቢያ ያለው የፓርክ፣ መጫወቻ ቦታ ወይም የጣሪያ ላይ ቦታ ላይ ደህንነት ላለው ጨዋታ መደበኛ እድሎች እንደሚሰጧቸው ሊያረጋግጥ ይገባል።

ይህ የመጫወቻ ቦታ በሚከተለው ቦታ ላይ መሆን አለበት፥

- የተቋሙ ግቢ ውስጥ የታጠረ ቦታ ላይ፤
- በቅራቢያ ያለው ፓርክ ወይም የመጫወቻ ቦታ፤ ወይም
- የፍቃድ መስጫ መሰርቶችን የሚያሟላ የጣሪያ ላይ የመጫወቻ ቦታ።

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1, 163፥

# የቤት ውጭ ቦታ

የቦታ-ላይ የቤት ውጪ ተግባር ቦታዎች የሚከተሉት ሊኖራቸው ይገባል፥

- 60 ስኩዌር ጫማ በአንድ ልጅ
- መውደቅን የሚቋቋሙ ቁሳቁሶች (ማለትም፣ የእንጨት ቁራጮች፣ የጎማ ላስቲክ ንጣፍ፣ ወዘተ.)
- በ US የተጠቃሚ ምርት ደንነት ኮሚሽን/ የአሜሪካ ማህበረሰብ ለምርመራ እና ቁሳቁሶች የተቋቋሙ መስፈርቶችን የሚከተል ለእድሜ-ተገቢ የሆነ መሳሪያ
- በአጥር ወይም በተፈጥሮ ከለላ የታጠረ አካባቢ ቢያንስ የ4 ጫማ ቁመት፣ ከታችኛው ጠርዝ እና መሬት መካከል 3.5 ኢንች ያልበለጠ ቦታ ያለው

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1, 163፥

# የሠራተኛው ብቃቶች

# የማዕከል ዳይሬክተር

የሚከተሉት መስፈርቶች በሁሉም የልጅ እድገት ተቋማት ላይ ተግባራዊ ይሆናሉ፥

- የማእከል ዳይሬክተር አብዛኞቹ ህጻናት በሚኖሩበት የማእከሉ የከፍተኛ ስራ ሰዓታት ወቅት ሁል ጊዜ በተቋሙ ላይ በአካል መገኘት እና በተቋሙ ላይ የስራ ቀናት እና ትክክለኛ ሰዓታት መዝገብን በህንጻው ላይ መያዝ አለበት።
- የማእከሉ ዳይሬክተር ከተቋሙ ሊቀር ይችላሉ፣ እሱ/ሷ ፍቃድ ያለው የልጅ እድገት ተቋም ተወካይን ከወከለ፣ የማእከሉ ዳይሬክተር የሚቀርበት ወቅት በአካል በተቋሙ ላይ መገኘት ያለበት። ይህ ስልጣን ያለው ተወካይ ሁሉም የማእከል ዳይሬክተር የብቃት መስፈርቶችን ማሟላት እና በማእከል ዳይሬክተሩ መቅረት ወቅት ሙሉ የተቋሙ የአስተዳደር እና የአሰራር ሀላፊነትን መውሰድ አለበት።

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1, 164.10

# የማዕከል ዳይሬክተር ብቁነት

የማእከል ዳይሬክተር ከሚከተሉት የብቃት መስፈርቶች አንዱን ማሟላት አለባቸው፥

- በUS የትምህርት ዋና ጸሀፊ ወይም የከፍተኛ ትምህርት የምስክር ወረቀት መስጫ ምክር ቤት እውቅና ያገኙ ኤጀንሲዎች የምስክር ወረቀት ካለው ተቋም የባችለር ዲግሪ ወይም የበለጠ የላቀ ዲግሪን ማግኘት፣ በቀደመ የልጅነት እድገት፣ የቀደመ ልጅነት (ኤርሊ ቻይልድሁድ) ትምህርት፣ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም የቀደመ ልዩ ትምህርት ቢያንስ 15 የሴምስተር ክሬዲት ሰዓታት፣ ወይም እውቅና ያለው ተመዛዢ ጋር፣ እና ፍቃድ ያለው የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የልጅ እድገት ማዕከል ወይም በሌላ ግዛት ውስጥ ተመዛዢ ውስጥ ከልጆች ጋር በመስራት ቢያንስ የአንድ ዓመት ቁጥጥር የተደረገበት ልምድ ያላቸው፤

- በUS የትምህርት ዋና ጸሀፊ ወይም የከፍተኛ ትምህርት የምስክር ወረቀት መስጫ ምክር ቤት እውቅና ያገኙ ኤጀንሲዎች የምስክር ወረቀት ካለው ተቋም ተባባሪ ዲግሪ ማግኘት፣ በቀደመ የልጅነት እድገትወይም የቀደመ ልጅነት (ኤርሊ ቻይልድሁድ) ትምህርትን በዋናነት ያጠኑበት፣ እና ፍቃድ ያለው የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የልጅ እድገት ማዕከል ወይም በሌላ ግዛት ውስጥ ተመዛዢ ውስጥ ከልጆች ጋር በመስራት ቢያንስ የሶስት ዓመት ቁጥጥር የተደረገበት ሙያዊ ልምድ ያላቸው፤ እና በንዑስ-ክፍል 164.1(a) ውስጥ እንደተገለጸው፣ እሱ/ሷ የዚህ ምዕራፍ ተግባራዊ ቀን በኋላ በስድስት ዓመታት ውስጥ የባችለር ዲግሪ ወይም የበለጠ የላቀ ዲግሪን እስካገኙ ድረስ፤

5A DCMR ምዕራፍ 1, 164፥

# የማዕከል ዳይሬክተር ብቁነት

የማእከል ዳይሬክተር ከሚከተሉት የብቃት መስፈርቶች አንዱን ማሟላት አለባቸው፥

- በUS የትምህርት ዋና ጸሀፊ ወይም የከፍተኛ ትምህርት የምስክር ወረቀት መስጫ ምክር ቤት እውቅና ያገኙ ኤጀንሲዎች የምስክር ወረቀት ካለው ተቋም ቢያንስ 48 ክሬዲት ሰዓታትን ያገኙ፣ በቀደመ የልጅነት እድገት ወይም የቀደመ ልጅነት (ኤርሊ ቻይልድሁድ) ትምህርት ቢያንስ 15 የሴምስተር ክሬዲት ሰዓታት፣ ወይም እውቅና ያለው ተመዛዥ ጋር፣ እና ፍቃድ ያለው የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የልጅ እድገት ማዕከል ወይም በሌላ ግዛት ውስጥ ተመዛዥ ውስጥ ከልጆች ጋር በመስራት ቢያንስ የአራት ዓመት ቁጥጥር የተደረገበት ሙያዊ ልምድ ያላቸው፤ በእነዚህ ደንቦች ተፈጻሚነት ቀን ላይ ፍቃድ ያለው የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የልጅ እድገት ማዕከል ውስጥ እንደ ብቁ የሆነ የማዕከል ዳይሬክተር የተቀጠሩ፣ የማዕከል ዳይሬክተሩ የእነዚህ ደንቦች ተፈጻሚነት ቀን በኋላ ስድስት ዓመታት ያልበለጠ ጊዜ ውስጥ በ(a) ወይም (b) እስከ ታዘዙ ድረስ፤ ወይም
- ለሞንቴሶሪ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር፣ በሞንቴሶሪ የምስክር ወረቀት መስጫ ኮሚሽን ለመምህራን ትምህርት፣ ብሔራዊ ማዕከል ለሞንቴሶሪ ትምህርት፣ የአሜሪካ ሞንቴሶሪ ማህበር፣ ወይም የሞንቴሶሪ ዓለም-አቀፍ ማህበር የምስክር ወረቀት ባለው ፕሮግራም የሞንቴሶሪ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለባቸው፣ እና ፍቃድ ያለው የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የልጅ እድገት ማዕከል ወይም በሌላ ግዛት ውስጥ ተመዛዥ ውስጥ ከልጆች ጋር በመስራት ቢያንስ የሶስት ዓመት ቁጥጥር የተደረገበት ሙያዊ ልምድ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል።

5A DCMR ምዕራፍ 1, 164፥

# የመምህር ብቁነት

የልጅ እድገት ማእከል ውስጥ ያለው መምህር ቢያንስ 18 ዓመት እድሜ መሆን እና የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ አለባቸው፥

- በቀደመ የልጅነት ትምህርት፣ የቀደመ የልጅነት እድገት፣ የልጅ እና የቤተሰብ ጥናቶች ወይም በቅርብ ተያያዥነት ያላቸው ፊልዶችን በዋናነት (ሜጀር) የሚያስተምር ተባባሪ ወይም የበለጠ የላቀ ድግሪን በዩናይትድ ስቴትስ የትምህርት ዋና ጸሀፊ ወይም የከፍተኛ ትምህርት ምስክር ወረቀት መስጫ ምክር-ቤት እውቅና ያገኘ ኤጀንሲ የምስክር ወረቀት ካገኘ ተቋም ማግኘት፤

- በUS የትምህርት ዋና ጸሀፊ ወይም የከፍተኛ ትምህርት የምስክር ወረቀት መስጫ ምክር ቤት እውቅና ያገኙ ኤጀንሲ የምስክር ወረቀት ካለው ተቋም ተባባሪ ወይም የበለጠ የላቀ ዲግሪን ያገኙ፣ በቀደመ የልጅነት እድገት ወይም የቀደመ ልጅነት (ኤርሊ ቻይልድሁድ) ትምህርት፣ ወይም የልጅ እና የቤተሰብ ጥናቶች ውጪ በሆነ ፊልድ በዋናነት (ሜጀር) ቢያንስ 24 የሴምስተር ክሬዲት ሰዓታት፣ ወይም እውቅና ያለው ተመዛዢኙ ጋር ያገኙ፣ እና በቀደመ የልጅነት እድገት ወይም የቀደመ ልጅነት (ኤርሊ ቻይልድሁድ) ትምህርት፣ ወይም የልጅ እና የቤተሰብ ጥናቶች ፊልድ በUS የትምህርት ዋና ጸሀፊ ወይም የከፍተኛ ትምህርት የምስክር ወረቀት መስጫ ምክር ቤት እውቅና ያገኙ ኤጀንሲ የምስክር ወረቀት ካለው ተቋም ያገኙ፣ እና ፍቃድ ያለው የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የልጅ እድገት ማዕከል ወይም በሌላ ግዛት ውስጥ ተመዛዣኙ ውስጥ ከልጆች ጋር በመስራት ቢያንስ የአንድ ዓመት ቁጥጥር የተደረገበት ሙያዊ ልምድ ያላቸው

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1, 165፥

# የመምህር ብቁነት

የልጅ እድገት ማእከል ውስጥ ያለው መምህር ቢያንስ 18 ዓመት እድሜ መሆን እና የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ አለባቸው፥

- በUS የትምህርት ዋና ጸሀፊ ወይም የከፍተኛ ትምህርት የምስክር ወረቀት መስጫ ምክር ቤት እውቅና ያገኙ ኤጀንሲዎች የምስክር ወረቀት ካለው ተቋም ቢያንስ 48 ክሬዲት ሰዓታትን ወይም እውቅና ያለው ተመዛዛኙን ያገኙ፣ ከእነዚህ 15 የሴምስተር ሰዓታት ወይም እውቅና ያለው ተመዛዛኙ በቀደመ የልጅነት እድገት ወይም የቀደመ ልጅነት (ኤርሊ ቻይልድሁድ) ትምህርት፣ ወይም የልጅ እና የቤተሰብ ጥናት የሆነው፣ እና ፍቃድ ያለው የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የልጅ እድገት ማዕከል ወይም በሌላ ግዛት ውስጥ ተመዛዛኙ ውስጥ ከልጆች ጋር በመስራት ቢያንስ የሁለት ዓመት ቁጥጥር የተደረገበት ሙያዊ ልምድ ያላቸው፤ እሱ/ሷ በ(a) ወይም (b) ውስጥ እንደተገለጸው እስከ **ዲሴምበር 2. 2023** ድረስ ተባባሪ ዲግሪ እስካገኙ ድረስ፣

- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ ወይም ተመዛዛኙን እና ወቅታዊ የልጅ እድገት ተባባሪ (Child Development Associate) (CDA) የምስክር ማስረጃን ያገኙ፣ ግለሰቡ ለተመደበው የእድሜ ምደባ ብቁ እንደሚሆኑ የሚገልጽ፤ እሱ/ሷ በ(a) ወይም (b) ውስጥ በተገለጸው መሰረት እስከ **ዲሴምበር 2. 2023** ድረስ ተባባሪ ዲግሪ እስካገኙ ድረስ።

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1, 165፥

# የመምህር ብቁነት

የልጅ እድገት ማእከል ውስጥ ያለው መምህር ቢያንስ 18 ዓመት እድሜ መሆን እና የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ አለባቸው፥

- ለሞንቴሶሪ ትምህርት ቤት መምህር፣ በUS የትምህርት ዋና ጸሀፊ ወይም የከፍተኛ ትምህርት የምስክር ወረቀት መስጫ ምክር ቤት እውቅና ያገኙ ኤጀንሲዎች የምስክር ወረቀት ካለው ተቋም ተባባሪ ዲግሪን ማግኘት፣ እና በብሔራዊ ማዕከል ለሞንቴሶሪ ትምህርት፣ የአሜሪካ ሞንቴሶሪ ማህበር፣ ወይም የሞንቴሶሪ ዓለም-አቀፍ ማህበር፣ ወይም በሞንቴሶሪ የምስክር ወረቀት መስጫ ኮሚሽን ለመምህራን ትምህርት የምስክር ወረቀት ከተሰጠው ፕሮግራም የሞንቴሶሪ ምስክር ወረቀት ሊሰጣቸው ይገባል።

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1, 165፥

# የረዳት መምህር ብቁነት

የልጅ እድገት ማእከል ውስጥ ተባባሪ መምህር ቢያንስ 18 ዓመት እድሜ መሆን እና የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ አለባቸው፥

- በUS የትምህርት ዋና ጸሀፊ ወይም የከፍተኛ ትምህርት የምስክር ወረቀት መስጫ ምክር ቤት እውቅና ያገኘ ኤጀንሲ የምስክር ወረቀት ካለው ተቋም ተባባሪ ወይም የበለጠ የላቀ ዲግሪን ማግኘት፤
- ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ ወይም ተመዛዛኙን፣ እና ወቅታዊ የልጅ እድገት ተባባሪ (Child Development Associate) (CDA) የምስክር ማስረጃን ያገኙ፣ እሱ/ሷ ለሚሰሩበት የእድሜ ምደባ እንደ ተባባሪ መምህር ለማገልገል ግለሰቡ ብቁ መሆናቸውን የሚገልጽ፤
- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ ወይም ተመዛዛኙን፣ በቀደመ የቀደመ ልጅነት (ኤርሊ ቻይልድሁድ) ትምህርት ወይም የቀደመ ልጅነት (ኤርሊ ቻይልድሁድ) እድገት መስኮች ስልጣን ካለው የሙያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የስልጠና እና የብቃት ማረጋገጫ ማግኘት፤ እሱ/ሷ የCDA የምስክር ማስረጃን እስከ **ዲሴምበር 2, 2023** እስካገኙ ድረስ።

5A DCMR ምዕራፍ 1, 166፥

# የረዳት መምህር ብቁነት

የልጅ እድገት ማእከል ውስጥ ረዳት መምህር ቢያንስ 18 ዓመት እድሜ መሆን እና የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ አለባቸው፥

- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ ወይም ተመዛዛኙን ማግኘት፣ እና ፍቃድ ያለው የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የልጅ እድገት ማዕከል ወይም በሌላ ግዛት ውስጥ ተመዛዛኙ ውስጥ ከልጆች ጋር በመስራት ቢያንስ የአንድ ዓመት ቁጥጥር የተደረገበት ሙያዊ ልምድ ያላቸው፣ እሱ/ሷ የCDA የምስክር ማስረጃን እስከ **ዴሴምበር 2, 2023** እስካገኙ ድረስ።
- ለሞንቴሶሪ ትምህርት ቤት ረዳት መምህር፣ ቢያንስ የ20 ሰዓታት የሞንቴሶሪ ልዩ ስልጠና ማግኘት፣ ለትምህርት ቤቱ ልዩ የሆነ የገለጻ ፕሮግራምን ማጠናቀቅ፣ እና የሞንቴሶሪ ማስረጃ ያለው መሪ መምህር ቁጥጥር ስር መስራት አለባቸው።

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1, 166፣

# ተግባራዊ የሚደረግበት ቀናት እና የሚፈጸምበት የጊዜ ገደብ፥

**የሠራተኛ ብቃቶች፡** ለማእከል ዳይሬክሮች፣ መምህራን እና ረዳት መምህራን የአዲስ ሰራተኛ ብቃቶች በስራ መደቡ እና ያሁኑ የሠራተኛ ትምህርት ደረጃ መሰረት የተለያዩ የመገዛት ቀነ-ገደቦች አላቸው፥

- የማዕከሉ ርዕሰ መምህራን/ዳይሬክተሮች*፥ በቀደመ የልጅነት ጊዜ ትምህርት ባችለር ኦፍ አርት (ቢኤ) ዲግሪ ወይም እስከ **ዲሴምቤር 2, 2022** ድረስ ቢያንስ 15 ሴምስቴር ኪሬዲት ሃዎርስ የቀደመ በልጅነት ጊዜ ትምህርት ባችለር ዲግሪ ያለው

- መምህራን*፥ በቀደመ የልጅነት ጊዜ ትምህርት ተባባሪ ድግሪ ወይም በቀደመ የልጅነት ጊዜ ቢያንስ የ24 ሴሚስተር ኪሬዲት ሃዎር ያለውን ተባባሪ ዲግሪ እስከ **ዲሴምቤር 2, 2023** ማግኘት

- ረዳት አስተማሪዎች፡ CDA እስከ **ዴሴምበር 2፣ 2023**

*ደንቦቹ ላለፉት 10 ተከታታይ ዓመታት በእንደዚህ ዓይነት የስራ መደብ ላይ ለነበሩ ዳይሬክተሮች እና መምህራን የመታለፍ አማራጭን ያቀርባሉ።

# የሰራተኞች ምቹነት

ፍቃድ ተቀባይ፣ በእንክብካቤያቸው ውስጥ ያሉ ልጆች ጤና፣ ደህንነት እና ጤንነትን ለማሳደግ እና ለማረጋገጥ ቁርጠኛ የሆኑ ግለሰቦችን የያዘ ብቃት ያለው የሥራ-ሀይል መያዝ አለበት።

- በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተቀመጡ እነዚህን መስፈርቶች የሚያሟላ የመድሃኒት እና የአልኮል የምርመራ ፕሮግራም፣ በክፍል 2031 et seq. የ CYSHA (የዲሲ ሕግ 15-353፤ የዲሲ ኦፊሴላዊ ኮድ §§ 1-620.31 et seq.) ስር የሚታዘዝ።
- የትራፊክ መዝገቦች በሚመለከተው በሞተር ተሽከርካሪዎች መምሪያ አማካኝነት ይፈተሻሉ (የሚመለከተው ከሆነ)
- የወንጀል የኋላ ታሪክ ምርመራዎች እና የምቹነት ውሳኔ ሂደት፣ በ OSSE አማካኝነት(FBI፣ የስቴት ፖሊስ፣ ብሔራዊ የወሲባዊ አጥቃት መዝገብ፣ እና የልጅ ብዝበዛ እና የቸልተኝነት መዝገቦች)

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1፣ 132፤ 133፤ 134፥

# የወንጀል የኋላ ታሪክ ማጣሪያዎች

የፍቃድ ተቀባይ ያሁኑ ወይም እጩ የሰራተኛ አባል ምቹነት በOSSE በኩል በሚደረገው የጣት አሻራ እና የወንጀል ታሪክን በማጠናቀቅ መገምገም አለበት።

የወንጀል የኋላ ታሪክ ማጣሪያዎች የሚያካትቱት፥

- የ FBI የጣት-አሻራ ምርመራ፣ የቀጣይ ትውልድ መለያ (Next Generation Identification) በመጠቀም፤
- የብሔራዊ የወንጀል መረጃ ማዕከል ብሔራዊ የወሲባዊ ጥቃት መዝገብ ውስጥ በሚደረግ ፍለጋ፤ እና
- የሰራተኛ አባል የሚኖርበት ስቴት እና እንዲህ ያለ የሰራተኛ አባል ባለፉት አምስት ዓመታት የኖረበት እያንዳንዱ ስቴት ውስጥ የመዝገቦች፣ ማከማቻዎች ወይም ደታቤዞች ፍለጋ።

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1፣ 132፥

# የአደንዛዥ ዕጽ እና የአልኮል ምርመራ

ፍቃድ ተቀባዩ የሚከተሉትን የሚያቀርብ የግዴታ የአደንዛዥ እጽ እና አልኮል ምርመራ ፖሊሲዎችን እና አሰራሮችን ያቋቋማል፥

- ሁሉም የምርመራ ፕሮግራሞች ምርመራዎችን ያደርጋሉ፥
  1. ከመቀጠር በፊት፡
  2. የሠራተኛ ተገቢ የመታገድ ሪፈራል ላይ፤ እና
  3. የድህረ-አደጋ፣ ከአደጋ በኋላ በምክንያታዊነት በሚቻል ፍጥነት።
- በሌሎች የዲስትሪክት እና የፌዴራል ህጎች መገዛት የልጅ እድገት ተቋም ሰራተኞች ላይ በልዩ ሁኔታ ተግባራዊ ይሆናል።

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1, 136፥

# ስልጠናዎች እና የምስክር ወረቀት

- እያንዳንዱ የልጅ እድገት ተቋም ባሁን ጊዜ በCPR እና ለህጻናት የመጀመሪያ እርዳታ እና ተላላፊ በሽታዎችን መከላከል፣ መለየት እና ማስተዳደር ላይ ምስክር ወረቀት ያለው ቢያንስ ሁለት የሰራተኛ አባላትን ሁል ጊዜ ሊኖረው ይገባል።
- የድንገተኛ የጨቅላ ህጻናት ሞት ሲንድረም (Sudden Infant Death Syndrome) (SIDS) የሚመለከተው ከሆነ
- ምግብ የሚያስቀምጥ፣ የሚያዘጋጅ፣ የሚይዝ እና የሚያቀርብ ሰራተኛ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የመዘጋጃ ቤት ማረጋገጫዎች ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ የሚከተሉ መስፈርቶችን የመከተል ሀላፊነት አለበት፣ በመመለከተው የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ህጎች እና ደንቦች ስር እንደሚፈለገው ሁሉንም የሚጠየቁ ማረጋገጫዎች ወይም ፍቃዶች ማግኘትን በመጨመር።
- የምግብ ጥበቃ አስተዳዳሪ የምስክር ወረቀትን ከ DC Health ማግኘት

5A DCMR ምዕራፍ 1, 150.1፥

# የቁጥጥር መስፈርቶች

# ቁጥጥር

ልጆች በተቋሙ ውስጥ ባሉበት ወቅት ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል፤ ይህም ቁጥጥር የሚደረግባቸው ልጆች ሲተኙ፣ መጫወቻ ቦታው ላይ፣ በመስክ ጉዞዎች፣ በተሽከርካሪ ወይም ከተሽከርካሪ ውጪ በሚደረጉ ሽርሽሮች፣ እና በሁሉም የውሃ ጨዋታ እንቅስቃሴዎችን የሚያካትት፣ ግን በእነዚህ ብቻ ያልተገደበ፣ ሲሆን፣ በሁሉም ጊዜያት ሊያይዋቸው እና ሊሰሟቸው በሚችሉ ሃላፊነት ባላቸው ሠራተኞች እና በጎ ፈቃደኞች ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል።

5A DCMR ምዕራፍ 1, 120.1፥

# ቁጥጥር

- የአዋቂ-ለ-ልጅ ሬሾዎች እና የቡድን መጠኖች የሁሉም ልጆች ጤና እና ደህንነትን ለማረጋገጥ ይቋቋማሉ።
- በተጨማሪ፣ ልጆች በተቋሙ ውስጥ ባሉበት ወቅት ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል፤ ይህም ቁጥጥር የሚደረግባቸው ልጆች ሲተኙ፣ መጫወቻ ቦታው ላይ፣ በመስክ ጉዞዎች፣ በተሽከርካሪ ወይም ከተሽከርካሪ ውጪ በሚደረጉ ሽርሽሮች፣ እና በሁሉም የውሃ ጨዋታ እንቅስቃሴዎችን የሚያካትት ሲሆን ፣ በሁሉም ጊዜያት ሊያይዋቸው እና ሊሰሟቸው በሚችሉ ሃላፊነት ባላቸው ሠራተኞች እና በጎ ፈቃደኞች ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል።
- በዚህ ክፍል ውስጥ በሌላ መንገድ ከቀረበለት በስተቀር፣ በጎ ፈቃደኞች የአዋቂ-ለ-ልጅ ሬሾ መስፈርቶችን ለማሟላት ጥቅም ላይ ሊውሉ አይገባም። ለልጆች በቀጥታ እንክብካቤ ለማቅረብ፣ ወይም ለእነሱ ቁጥጥር ወይም መመሪያ ለመስጠት ሀላፊነት ያለባቸው ሰራተኞች ብቻ የአዋቂ-ለ-ልጅ ሬሾ ውስጥ የሚቆጠሩ ይሆናል።

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1, 120፥

# ቁጥጥር – የሰራተኛ ሽፋን

እያንዳንዱ የልጅ እድገት ማዕከል ለእያንዳንዱ ቡድን ሁል ጊዜ ቢያንስ ሁለት ሰራተኞች ሊኖሩት ይገባል።

- ዳይሬክተር እና መምህር
- መምህር እና ረዳት መምህር
- መምህር እና መምህር



5A DCMR ምዕራፍ 1, 121.8፥

# የቁጥጥር መስፈርቶች

ተቋሙ በዚህ ውስጥ እንደተገለጸው የአዋቂ-ለ-ልጅ ሬሾዎችን እና የቡድን መጠኖችን መጠበቅ አለበት፡

| የልጆች እድሜ | የአዋቂ/ልጅ ሬሾ | ከፍተኛ የቡድን መጠን |
|---|---|---|
| 0-24 ወራት | 1:4 | 8 |
| 24-30 ወራት | 1:4 | 12 |
| 30-48 ወራት | 1:8 | 16 |
| 48-60 ወራት | 1:10 | 20 |

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1, 121.3፥

# የሬሾ መስፈርቶች

- የተለያዩ እድሜ ያላቸው ህጻናት በአንድ ቡድን ውስጥ ሲጣመሩ፣ ለትንሹ ልጅ የአዋቂ/ልጅ ሬሾ ተግባራዊ ይሆናል በንዑስ ክፍል 121.10 እና 121.13 እስከ 121.15 ውስጥ እንደቀረበው ከሆነ በስተቀር።

- ምንም እንኳ በቡድኑ ውስጥ ከፍተኛ የልጆች ቁጥር ባይኖርዎትም፣ ሁል ጊዜ ቢያንስ ለእያንዳንዱ ቡድን ቢያንስ ሁለት አባላት ሊኖሩ ይገባል።

5A DCMR ምዕራፍ 1, 121.6፥

# የሬሾ መስፈርቶች

ህጋዊ ለትምህርት የደረሰ እድሜ ላላቸው ልጆች ከትምህርት-ቤት-ውጪ ጊዜ እንክብካቤን ለሚያቀርቡ ማእከላት፥

| የልጆች እድሜ | የአዋቂ/ልጅ ሬሾ | ከፍተኛ የቡድን መጠን |
|---|---|---|
| ከ6 ዓመት በታች | 1:12 | 24 |
| 6 ዓመት እና ከዚያ በላይ | 1:12 | 30 |

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1, 121.3 (b)

# የጤና፣ የደህንነት እና የጤንነት መስፈርቶች

# የጤና፣ የደህንነት እና የጤንነት መስፈርቶች

እያንዳንዱ የልጅ እድገት ተቋም የዳይፐር-መቀየሪያ ቦታን መለየት አለበት፣ ለሞቀ የቧንቧ ውሃ ምንጭ እና ሰሙና እንዲቀርብ እና የተቋሙ የወጥ ቤት አካባቢ እንዳይሆን።



5A DCMR፣ ምዕራፍ 1, 145፥

# የጤና፣ የደህንነት እና የጤንነት መስፈርቶች

እያንዳንዱ የልጅ እድገት ተቋም የእጅ መታጠብን በተመለከተ የተጻፈ ፖሊሲን ማስቀመጥ፣ ማስፈጸም እና ማሳየት አለበት፣ የሚከተሉትን የሚያስተናግድ፥

- ለሠራተኞች እና ለልጆች የእጅ መታጠብ መቼ እንደሚያስፈልግ
- ልዩ ልዩ የእጅ መታጠቢያ አሰራሮች



5A DCMR፣ ምዕራፍ 1, 144፥

# አልጋዎች እና የህጻናት አልጋዎች

እያንዳንዱ የልጅ እድገት ተቋም የሙሉ ቀን ፕሮግራም ውስጥ ለተመዘገቡ እያንዳንዱ ልጅ የግል አልጋዎችን ማቅረብ አለበት።

- ህጻናት አልጋ ላያጋሩ ይችላሉ።
- አንሶላ ሁል ጊዜ ንጹህ እና ጽዱ ሆኖ መያዝ አለበት።
- የህጻናት አልጋዎች ከመጫወቻ ቦታ በበቂ ሁኔታ መራቅ አለበት።
- ጥቅም ላይ ሲሆኑ፣ እያንዳንዱ አልጋ ከሌላ አልጋ 2 ጫማ መራቅ፣ ከመስኮት 2 ጫማ መራቅ፣ እና በሁሉም ጎኖች ከራዴየተሮች 2 ጫማ መራቅ አለበት።

ብርድ ልብሶች በተቋሙ ወይም የልጅ ቤተሰብ መቅረብ አለባቸው።

- ማንም ልጅ በባዶ ገላ፣ ሳይሸፈኑ መተኛት የለባቸውም።




5A DCMR ምዕራፍ 1, 126፥

# የሚያስፈልጉ የመጀመሪያ እርዳታ አቅርቦቶች

ለእያንዳንዱ 25 ልጆች፣ እያንዳንዱ ተቋም የሚያስፈልጉ የመጀመሪያ እርዳታ አቅርቦቶች መጓጓዝ የሚችል እና የማይችል መጠንን መያዝ አለበት።




5A DCMR፣ ምዕራፍ 1, 150፥

# የጤና፣ የደህንነት እና የጤንነት መስፈርቶች

- የልጅ እድገት ተቋም ማንም ሰው፣ ሰራተኞች፣ ወላጆች እና ጎብኚዎችን ጨምሮ፣ በፕሮግራም ቦታ ውስጥ ማጨስ ወይም የትንባሆ ምርቶችን እንደማይጠቀም ማረጋገጥ አለበት።
- በስራ ሰዓታት፣ ሁሉም የትንባሆ ምርቶች ሁል ጊዜ ከልጆች መዳረሻ ውጪ መቆየት አለባቸው።
- ልጆች በተቋሙ እንክብካቤ ውስጥ፣ ወይም ከቦታ-ውጪ ሲሆኑ፣ ማንኛውም የሰራተኛ አባላት የአልኮል መጠጦች መጠጣት ወይም በአልኮል ተጽዕኖ ስር መሆን ወይም ህጋዊ-ያልሆኑ መድሃኒቶችን መጠቀም የለባቸውም።

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1, 142፥

# የጦር መሳሪያዎች

ፍቃድ ተቀባዩ ምንም ዓይነት የጦር መሳሪያዎች ወይም ሌሎች መሳሪያዎች በተቋሙ ህንጻዎች ላይ እንደሌሉ ያረጋግጣል፣ ፍቃድ ያላቸው እና የተቋሙን ህንጻዎች ለመጠበቅ የታጠቀ የደህንነት ጠባቂ ይዞታ እና ቁጥጥር ውስጥ በአግባብ ካሉት በስተቀር።

5A DCMR ምዕራፍ 1, 142.7፥

# የማጓጓዣ መስፈርቶች

ልጆችን ለማጓጓዝ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሞተር ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት የያዘ፣ የሚጠቀም፣ ወይም የሚጠግን እያንዳንዱ የልጅ እድገት ተቋም የሞተር ተሽከርካሪዎች ጥገና እና መጠቀምን እና የልጆች ማጓጓዝን የሚያስተዳድሩ ሁሉም የሚመለከቱ የፌዴራል እና የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ህጎችን እና ደንቦችን መከተል አለባቸው።

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1, 158፥

# የማይፈቀዱ ቁሳቁሶች ምሳሌዎች

- የጨቅላ ህጻናት ማስኬጃዎች
- የህጻን አልጋ ጂሞች
- የምታጠፉ አልጋዎች
- የመጫወቻ ስክሪብቶ
- የሚወረወሩ አሻንጉሊቶች



5A DCMR ምዕራፍ 1, 126.5፥

# ግብአቶች እና ድጋፍ

# የፍቃድ መስጫ ደንቦች

እባክዎ ያስታውሱ፣ ይህ ገለጻ የማብራሪያ መረጃ እና መስፈርቶችን ያቀርባል፣ ግን ሁሉም የሚመለከታቸው ደንቦችን ለመረዳት DCMR ርዕስ 5A፣ ምዕራፍ 1 በጥንቃቄ ማንበብ አለብዎት ደንቦችን እዚህ ያንብቡ፥ osse.dc.gov/service/early-learning-regulations-and-policies

# ግብአቶች እና ድጋፍ

ለፍቃድ መስጫ ማመልከቻዎን ካስገቡ በኋላ፣ የፍቃድ መስጫ ስፔሻሊስት ይመደብልዎታል።

ለፈቃድ ሰጭ ስፔሺያሊስት የሚከተሉትን ያደርጋል፥

- ፍቃድ ለማግኘት ማመልከቻ ሲገባ የሚያስፈልጉ ሰነዶችን እና ሂደቶችን በተመለከተ ጥያቄዎችን ይመልሳል፤
- የልጅ እንክብካቤ ፍቃድ መስጫ ማመልከቻን ለመሙላት የሚያስፈልጉ ሌሎች ኤጀንሲዎችን በተመለከተ መረጃ ይሰጥዎታል፤ እና
- ፍቃድዎን ከመውሰድዎ በፊት ወይም በኋላ መመሪያ እና ቴክኒካዊ እርዳታን ያቀርባል።

የፍቃድ መስጫ ክፍልን ለማነጋገር፣ እባክዎ ወደ (202) 727-1839 ይደውሉ

# ግብአቶች እና ድጋፍ

ቅጾች እና ተጨማሪ መረጃ በ OSSE ድረገጽ ላይ መገኘት ይችላሉ።

- ፍቃድ መስጠት፦ osse.dc.gov/service/licensing-and-compliance
- ደንቦች እና ፖሊሲዎች፦ osse.dc.gov/service/early-learning-regulations-and-policies
- የፍቃድ መስጫ ደንቦች ማጠቃለያ፦ osse.dc.gov/publication/summary-and-overview-final-rulemaking-licensing-child-development-facilities
- ሙያዊ እድገት፦ osse.dc.gov/service/early-learning-services-providers-professional-development
- ጤናማ ቶትስ (Healthy Tots)፦ osse.dc.gov/node/1132611
- የድጎማ ፕሮግራም፦ osse.dc.gov/page/subsidy-program
- የECE የእርዳታ ጰሃፊ፦ ECEHelpdesk@dc.gov ወይም (202) 478-5903

# የፍቃድ መስጫ የጊዜ ገደብ

# የፍቃድ መስጫ የጊዜ ገደብ

- የፈቃድ መስጫ ሂደቱ በግምት ከአንድ እስከ ሶስት ወራትን ይወስዳል። አንድ አመልካች ፍቃድ የሚያገኝበት የጊዜ ገደብ የአመልከቻ መገኘት እና አመልካቹ ማንኛውም የተለዩ ጉድለቶችን ለማስተካከል የሚወስድበት የጊዜ ገደብ ላይ የተመሰረተ ነው።
- የፈቃድ መስጫ ሂደት እና የጊዜ ገደብ በሚከተለው ማፈንጠሪያ መገኘት ይችላል፥ osse.dc.gov/sites/default/files/dc/sites/osse/service_content/attachments/Licensing%20Process%20Graphic_3%20Year_Final.pdf

5A DCMR፤ ምዕራፍ 1, 103፥

# የፈቃድ አሰጣጥ ሂደትን ማሰስ

# የአጠቃላይ እይታ

የፈቃድ መስጫ ሂደት የሚከተሉ ደረጃዎች አሉት፥

- ኦሪየንቴሽን(ገለጻ) ማጠናቀቅ
- ፍቃዶችን እና የምስክር ወረቀቶችን ማግኘት
- ማመልከቻ እና ክፍያዎችን ማስገባት
- ለመጀመሪያ የቁጥጥር ምርመራ መዘጋጀት
- የመጀመሪያ የቁጥጥር ምርመራ
- ለክትትል ምርመራ መዘጋጀት (አስፈላጊ ከሆነ)
- የማረጋገጫ ጉብኝት
- የልጅ እድገት ተቋም ፍቃድ አሰጣጥ

# ደረጃ 1፥ ኦሪየንቴሽን(ገለጻ) ማጠናቀቅ

የፍቃድ መስጫ ደንቦች ገለጻ እና ግምገማን ማጠናቀቅ

- የኦንላይን የፍቃድ መስጫ ዌብናርን መመልከት።
- የገለጻ መጠይቅን በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ።
- የገለጻ ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀትን ማተም (ከመጀመሪያ ማመልከቻ ጋር ማስገባት)።
- ለልጅ እድገት ተቋም ፍቃድ መስጫ የማመልከቻ እሽግን መጀመር።

*እባክዎ ያስታውሱ፥ ልዩ ፍላጎቶች እና/ወይም የቋንቋ ተደራሽነት የሚያስፈልጋቸው እጩ አመልካቾች ከፈቃድ ሰጪ ቡድን ጋር የአንድ-ለአንድ ገለጻ እንዲደረግላቸው ቀጠሮ ማስያዝ ይችላሉ። ለበለጠ መረጃ እና ጥያቄዎች፣ እባክዎ የፈቃድ ሰጭ ቡድኑ ጋር በ (202) 727-1839 ይደውሉ እና በሥራ ላይ ያለውን የፈቃድ ሰጭ ስፔሺያሊስትን ለማነጋገር ይጠይቁ።

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1, 103፥

# ደረጃ 2፥ ፍቃዶችን እና የምስክር ወረቀቶችን ማግኘት

- የልጅ እድገት ተቋም **የይዞታ ፍቃድ የምስክር ወረቀት (COP)** ማግኘት አለባቸው።
- COP ወይም ሌላ ተከታይ ተመዛዛኝ ማረጋገጫ ቅጽ ያስፈልጋል፣ ህንጻው(ህንጻዎጾቹ) ሁሉም የሚመለከቱ የፌዴራል እና የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ግንባታ፣ የእሳት-አደጋ-ደህንነት፣ የግንባታ እና የዞን ማከፋፈያ ህጎችን፣ ደንቦችን እና ኮዶችን እንደሚከተል(ሉ) እና ህንጻው(ህንጻዎቹ) በተጠቃሚ እና ቁጥጥር ጉዳዮች (DCRA )ለወጣ የልጅ እድገት ተቋም አሰራር ብቁ እና ምቹ መሆኗቸውን የሚያረጋግጥ።

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1፣ 103.5 (a)

# ፍቃዶችን እና የምስክር ወረቀቶችን ማግኘት

COP ከሚከተለው መገኘት ይችላል፥

የተጠቃሚ እና የቁጥጥር ጉዳዮች መምሪያ ክፍል (DCRA)
Building and Land Regulation Administration (የህንጻ እና የመሬት ቁጥጥር አስተዳደር)
የዞን ማከፋፈያ ክፍል
1100 Fourth St. SW, Second Floor
ዋሽንግተን፣ ዲሲ 20024
dcra.dc.gov/node/1410111

የእርስዎን COP ቅጂን ለልጅ እድገት ተቋም ፍቃድ መስጫ ማመልከቻ ያያይዙ።

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1፣ 103.5 (a)

# ፍቃዶችን እና የምስክር ወረቀቶችን ማግኘት

**የእሳት-አደጋ ደንነት የቁጥጥር ምርመራ የምስክር ወረቀት**

የእሳት አደጋ ደህንነት የቁጥጥር ምርመራ የምስክር ወረቀት ከDCRA፣ የእሳት አደጋ ጥበቃ ቅርንጫፍ፣ እና የህንጻ እና የመሬት ቁጥጥር አስተዳደር መገኘት አለበት።

1100 Fourth St. SW, Second Floor
ዋሽንግተን፣ ዲሲ 20024
dcra.dc.gov/node/1410111

ለሙሉ የቦታ-ላይ የእሳት አደጋ መከላከያ ቁጥጥር እና የእሳት አደጋ ጊዜ ቤት ለቆ የመውጣት እቅድ ግምገማ ቀጠሮ ለመያዝየ የDCRA ተወካይ ያነጋግርዎታል።

የመጨረሻ የቁጥጥር ማጽደቂያ እና የእሳት አደጋ ጊዜ ቤት ለቆ የመውጣት እቅድ ቅጂን ከልጅ እድገት ተቋም የፍቃድ መስጫ ማመልከቻ ጋር ያያይዙ።

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1፣ 103.5 (b)

# ፍቃዶችን እና የምስክር ወረቀቶችን ማግኘት

**የሊድ ማረጋገጫ**

በዲሲ የሃይል አቅርቦት እና አካባቢ ጥበቃ መምሪያ (DC Department of Energy and Environment) (DOEE) ፍቃድ-ያለው ሊደ-መሰረት ያደረገ ተቆጣጣሪ፣ የአደጋ ስጋት ገምጋሚ ወይም የአብዋራ ናሙና ሰብሳቢ ቴክኒሻን የወጣው የማረጋገጫ ወይም የመልቀቂያ ወረቀት ሪፖርት፣ ተቋሙ ማንኛውም ሊደ-መሰረት ያደረጉ የቀለም አደገኛ ኬሚካሎች እንደሌለው የሚያረጋግጥ፣ እና ከማመልከቻው በፊት 30 ቀናት ያልበለጠ ውስጥ የወጣ።

ፍቃድ ያለው የሊድ የአደጋ ስጋት ገምጋሚ ዝርዝር በሚከተለው ሊገኝ ይችላል፥

የዲስትሪክቱ የሃይል አቅርቦት እና አከባቢ ጥበቃ መምሪያ
1200 First St. NE, Fifth Floor
Washington, DC 20002
doee.dc.gov/publication/individuals-certified-conduct-lead-based-paint-activities

የእርስዎን የሊድ ማረጋገጫ ቅጂን ለልጅ እድገት ተቋም ፍቃድ መስጫ ማመልከቻ ያያይዙ።

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1፣ 103.5 (c)

# ፍቃዶችን እና የምስክር ወረቀቶችን ማግኘት

**የንጹህ እጆች (ክሊን ሃንድስ) የምስክር ወረቀት**

አመልካች ከኮሎምቢያ ዲስትሪክት፣ በዲሲ ኦፊሴላዊ ኮድ § 47-2862 የስራ ፍቃድ ወይም ፍቃድ ለማግኘት ሊሟሉ የሚገቡ መስፈርቶችን እንደሚሟላ የሚያሳይ፣ እና ማመልከቻው ከገባው በኋላ በ30 ቀናት ውስጥ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የግብር እና ገቢዎች ቢሮ የወጣ የንጹህ እጆች (ክሊን ሃንድስ) የምስክር ወረቀት።

otr.cfo.dc.gov/page/certificate-clean-hands

የእርስዎን የንጹህ እጆች (ክሊን ሃንድስ) የምስክር ወረቀት ቅጂን ለልጅ እድገት ተቋም ፍቃድ መስጫ ማመልከቻ ያያይዙ።

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1፣ 103.5 (e)

# ፍቃዶችን እና የምስክር ወረቀቶችን ማግኘት

**መድን**

የመድን ማስረጃ፣ ተገቢ የሽፋን መጠን የሚያካትት፣ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የአደጋ ስጋት አስተዳደር ቢሮ እንደተወሰነው፣ ለሚከተለው የሽፋን ዓይነት፥

1. የንግድ የጠቅላላ ተጠያቂነት፤
2. የጥላ "የክትትል ቅጽ" ተጠያቂነት፤
3. የወሲባዊ ጥቃት እና ብዝበዛ ተጠያቂነት፤ እና
4. በተቋሙ ውስጥ ለልጆች የመጓጓዣ አገልግሎቶችን ለማቅረብ ጥቅም ላይ የሚውል እያንዳንዱን ተሽከርካሪ የሚሸፍን የተሽከርካሪ ተጠያቂነት (የሚመለከተው ከሆነ)።

የእርስዎን የመድን ማረጋገጫ ቅጂን ለልጅ እድገት ተቋም ፍቃድ መስጫ ማመልከቻ ያያይዙ።

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1፣ 103.5 (f)

# ፍቃዶችን እና የምስክር ወረቀቶችን ማግኘት

**የህንጻ አጠቃቀም ስምምነት**

የቅድሚያ የስራ ቦታ ለማግኘት ከተቋረጠ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል የድንገተኛነት ቦታን የሚለይ ወቅታዊ፣ ተቀባይነት ያለው እና የተረጋገጠ የህንጻ መጠቀሚያ ስምምነት፣ የሚከተሉትን የሚያካትት፣ ግን በዚህ ብቻ ያልተገደበ፥

- የህንጻው ባለቤት የመገኛ መረጃ፤
- የሚጠቀሙበት ዓላማ፥
- አጠቃላይ መመሪያዎች እና መስፈርቶች፤
- ተገቢ የመድን ሽፋን ማስረጃ፤
- ተቀባይነት ያለው የይዞታ ምስክር ወረቀት ማስረጃ፤
- የተሻሻለው ለልጅ የእድገት ተቋም ልዩ የሆነ የደህንነት ምርመራዎች ማስረጃ፤
- የተጠቃሚ ሃላፊነቶች፤ እና
- የተጠቃሚ ገደቦች፤ እና የተቋም አጠቃቀም ክፍያ፣ ካለ።

በህንጻ መጠቀም ስምምነት ውስጥ፣ አመልካች ከ24 ሰዓታት በላይ የድንገተኛ ሁኔታ ሲኖር ተቋሙን ለመዝጋት ሊመርጥ ይችላል፣ የተቋም መዝጋት መግለጫ ወረቀትን ከ "ደህንነት ያለው ቦታ ለቆ መውጣት" ቅጽ እና ከማመልከቻቸው ጋር በማያያዝ።

የእርስዎን የህንጻ መጠቀም ስምምነት ቅጂን ለልጅ እድገት ተቋም ፍቃድ መስጫ ማመልከቻ ያያይዙ።

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1፣ 103.5 (g)

# ደረጃ 3፥ ማመልከቻ ማስገባት

**የመጀመሪያ የማመልከቻ ማስገባት የሚከተሉትን ማካተት አለበት፥**

- የተሞላ የማመልከቻ ቅጽ
- የገለጻ ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት ቅጂ
- የመጀመሪያ የይዞታ ሰርተፊኬት
- የመጀመሪያ የጸደቀ የእሳት-አደጋ ጊዜ ቤት ለቆ መውጣት እቅድ
- የመጀመሪያ የሊድ ቁጥጥር የምስክር ወረቀት - ወይም ሪፖርት
- የንጹህ እጆች (የክሊን ሃንድስ) ሰርተፊኬት
- ወቅታዊ የተጠያቂነት መድን ሽፋን ማስረጃ
  1. የንግድ የጠቅላላ ተጠያቂነት
  2. የጥላ "የክትትል ቅጽ" ተጠያቂነት
  3. የወሲባዊ ጥቃት እና ብዝበዛ ተጠያቂነት
  4. የተሽከርካሪ ተጠያቂነት (የሚመለከተው ከሆነ)

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1, 103.4፥

# ማመልከቻ ማስገባት

**የመጀመሪያ የማመልከቻ ማስገባት የሚከተሉትን ማካተት አለበት፥**

- የጥሩ ቁመና የምስክር ወረቀት (ተካቶ ከሆነ)
- የመጀመሪያ የማመልከቻ/የቅድመ-ፍቃድ መስጫ ቁጥጥር ልፍያ (ለ DC ሀብት መያዣ እንዲከፈል የተደረገ)
- የወንጀል የኋላ ታሪክ ፍተሻዎች እና ታሪኮች ለአመልካች፣ የሚጨምሩት፥
  1. የፌዴራል የምርመራዎች ቢሮ ፍትሻ ውጤቶች ለመልካች፤
  2. የልጅ ጥበቃ ምዝገባ ማጣሪያው ውጤቶች
- የሰራተኛ ማስረጃዎች (በዚህ ጊዜ ተቀጥረው ከሆነ)

# ማመልከቻ ማስገባት

**የፍቃድ መስጫ ማመልከቻ እሽጎች ከክፍያው ጋር መግባት አለባቸው፣ ለ፥**

የስቴት ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ
የቀደመ ትምህርት ክፍል
የልጅ እድገት ፍቃድ መስጫ ክፍል
1050 First St. NE, Sixth Floor
Washington, DC 20002

# የመጀመሪያ ምርመራ

# ደረጃ 4፥ ለመጀመሪያ የቁጥጥር ምርመራ መዘጋጀት

የፍቃድ መስጫ ስፔሻሊስት ማመልከቻዎ ከደረሰ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ ያነጋግርዎታል። አስፈላጊ ሰነዶችን ለመጫን የቀደመ ትምህርት ፍቃድ መስጫ መሳሪያ (Division of Early Learning Licensing Tool) (DELLT) ተደራሽነት ይፈቀድልዎታል።

የሚከተሉ ሰነዶችን ለግምገማ ይጫኑ፥

- የጽሁፍ ፕሮግራም፣ ፖሊሲዎች እና አሰራሮች
- የአልኮል እና የአደንዛዥ እጽ ፖሊሲዎች እና የምርመራ አሰራሮች
- የህንጻ መጠቀም ስምምነት ወይም ከቦታ በደህንነት ለቆ የመውጣት ቅጽ
- የUSDA የልጅ እና የአዋቂ ቅጽ የምግብ ፕሮግራም የምሳ አበላል አሰራርን የሚከተል የናሙና የአምስት-ቀን ሜኑ (ምግብ የሚያቀርቡ ከሆነ)

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1, 103.7፥

# ለመጀመሪያ የቁጥጥር ምርመራ መዘጋጀት

- ለተመዘገቡ የልጆች ቁጥር በቂ የሆኑ ለእድገት አግባብ የሆኑ ቁሳቁሶችን፣ መሳሪያዎችን፣ ኮቶች/የሕፃን አልጋዎች መግዛት።
- የፕሮግራም ቦታ(ዎች)ን መለየት እና ለልጆች የፕሮግራም መማሪያ/እንቅስቃሴ አካባቢያዎችን ማዘጋጀት።
- የሚከተሉትን የያዙ የሰራተኞች ፋይሎችን ማሟላት፦
  - ወቅታዊ የጤና የምስክር ወረቀት፤
  - የሠራተኛ የጤና መረጃ ቅጽ፤
  - የሠራተኛ መቀጠር ቅጽ፤
  - ትምህርታዊ የምስክር ወረቀቶች፣ ሪዘሜ፤
  - የወንጀል እና የኋላ ታሪክ ምርመራዎች፣ በOSSE-የወጣ የምቹነት ማስታወቂያ፤
  - የአደንዛዥ እጽ እና አልኮል ፖሊሲዎች እና የቅድመ-ቅጥር ፈተና ውጤቶች፤
  - የድንገተኛ የጨቅላ ህጻናት ሞት ሲንድረም (SIDS) ስልጠና፤
  - የመጀመሪያ እርዳታ እና የCPR ማረጋገጫ፤ እና
  - የትራፊክ መዝገብ ፍተሻ (ሠራተኛ ልጆችን የሚያጓጉዝ ከሆነ ብቻ ያስፈልጋል)።

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1, 130, 131, 132፦

# ደረጃ 5፥ የመጀመሪያ ምርመራ

በመጀመሪያው ቁጥጥር ወቅት፣ የፍቃድ መስጫ ስፔሺያሊስት፥

- ሁሉም የጤና፣ የደህንነት እና የፍቃድ መስጫ መስፈርቶች እንደተሟሉ ለማረጋገጥ ተቋምዎ ላይ የቁጥጥር ምርመራ ያደርጋል፤
- ለመጀመሪያ ቁጥጥር በአመልካች የገቡ ሁሉንም ሰነዶች ይገመግማል፤ እና
- የጉድለቶች መግለጫ ሪፖርን ያወጣል፣ የሚመከር የማስተካከያ እቅድ ጋር (የሚመለከት ከሆነ)።

አመልካች፣ በOSSE እንደተለየው፣ 90 ቀናት ባልበለጠ ውስጥ፣ ጉድለቶችን በተጠየቀው ጊዜ ውስጥ ማስተካከል አለበት (የሚመለከት ከሆነ)።

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1, 103፥

# የክትትል ምርመራ

# ደረጃ 6፥ የክትትል ምርመራ

የክትትል ምርመራ ለማድረግ ቀጠሮ ለመያዝ የፍቃድ መስጫ ስፔሻሊስትዎን ያነጋግሩ፣ አስፈላጊ ከሆነ። በክትትል ምርመራ ወቅት፣ የፍቃድ መስጫ ስፔሻሊስትዎ በመጀመሪያው ቁጥጥር ማድረጊይዝ ጊዜዎ የተስተዋሉ ማንኛውም ጉድለቶችን ይገመግማል።

5A DCMR፣ ምዕራፍ 1, 103.9፥

# የፍቃድ መስጫ የማረጋገጫ ጉብኝት

# ደረጃ 7፥ የማረጋገጫ ጉብኝት

የመጀመሪያው ፍቃድ ከመውጣቱ በፊት የእርስዎ የፍቃድ መስጫ ስፔሻሊስት እና የፕሮግራም አስተዳዳሪ ለአንድ የመጨረሻ የቦታ-ቁጥጥር ተቋሙን ይጎበኛሉ።

# የፍቃድ መስጫ ክፍልን ያነጋግሩ

**አድራሻ፥**

1050 First St. NW, Sixth Floor

Washington, DC 20002

**የአድራሻ መረጃ፡**

- ክሌመንት ኢዱን፣ የፍቃድ መስጫ የፕሮግራም አስተዳዳሪ
  - Clement.Idun@dc.gov
  - (202) 442-4733
- ኢቫ ላጉኤሬ፣ የፍቃድ መስጫ እና የመታዘዝ ዳይሬክተር
  - Eva.Laguerre@dc.gov
  - (202) 741-5942
- ካሮሊን ቴይለር፣ የመታዘዝ የፕሮግራም አስተዳዳሪ
  - Carolyn.Taylor@dc.gov
  - (202) 727-8140
- ቶሚ ቶቴን፣ የፍቃድ መስጫ ጥራት የፕሮግራም አስተዳዳሪ
  - Tommy.Totten@dc.gov
  - (202) 442-5860

የገለጻ መጠይቅ

# ግንዛቤዎን ይፈትሹ

ከታች ያለው ማስፈንጠሪያ ላይ በመጫን ፈተናውን ያግኙ፥

[የኦንላይን የግንዛቤ ፈተና]

እናመሰግናለን!